City of Dallas

Office of Community Police Oversight

# መብቶችዎን ይወቁ፦ በDallas ውስጥ የሚገኙ ቅሬታ የማቅረብ መብቶች

**The Office of Community Police Oversight (OCPO) (የማኅበረሰብ ፖሊስ ቁጥጥር ጽሕፈት ቤት) ከፖሊስ ጋር የተያያዙ የሥነ-ምግባር ጥሰት ውንጀላዎችን በገለልተኝነት በመመርመር በማኅበረሰቡ፣ በDallas ከተማ አስተዳደር እና በDallas Police Department (DPD) (የDallas ፖሊስ አገልግሎት መምሪያ) መካከል ያለውን ተዓማኒነት ለማሳደግ ይሠራል። ሥነ-ምግባር የጎደለው ድርጊት በፖሊስ ተፈጽሞብኛል ብለው ካሰቡ OCPO እርስዎን መርዳት ይችል ይሆናል።**

## OCPO የDPD አካል ነው?

አይደለም፤ OCPO በሲቪል ዜጎች የሚመራ እና ገለልተኛ የሆነ ኤጀንሲ ሲሆን፣ እንቅስቃሴዎቹም ከDPD የተነጠሉ ናቸው።

## ቅሬታዎች መቅረብ ያለባቸው ክስተቱ ከተፈጠረ በምን ያህል ቀናት ውስጥ ነው?

ሁሉም ቅሬታዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ሲሆን፣ እንደቀረቡ ግምገማ ይደረግባቸዋል። በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ሪፖርት የተደረገው ክስተት ከተፈጠረ 60 ቀናት ካለፉ በኋላ ከሠራተኞች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ምርመራ አይደረግባቸውም፦

- ቅሬታው የወንጀል ድርጊትን የሚመለከት ከሆነ የወንጀል ሕጉ የሚያስቀምጠው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል። ይሁን እንጂ የመምሪያውን ታማኝነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ የይርጋ ጊዜው የDallas Police Departmentን የዲሲፕሊን እርምጃ ከመውሰድ አያግድም።
- ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያት አሳማኝ ከሆነ።

## በወቅቱ እስር ቤት ውስጥ ከሆንኩ ቅሬታ የማቅረብ መብት አለኝ?

አዎ፤ በወቅቱ እስረኛ መሆንዎ ቅሬታ የማቅረብ መብትዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም። የእኛ መርማሪ ወይም የDPD Internal Affairs Division (የውስጥ ጉዳዮች ክፍል) መርማሪ ቅሬታ አቅራቢዎችን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የከተማ ወይም የካውንቲ እስር ቤቶችን መጎብኘት ይችላሉ። ወይም ቅሬታዎን ወደ ጽሕፈት ቤታችን በፖስታ መላክ ይችላሉ።

## እንደ ሶስተኛ ወገን ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል?

አይቻልም፤ እንደ ሶስተኛ ወገን ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታ ማቅረብ አይችሉም። ከሶስተኛ ወገን የቀረቡ ክሶች በInternal Affairs Division ፍላጎት መሠረት ምርመራ ሊደረግባቸው ይችላል። እነዚህ ክሶች በጽሑፍ መልክ የተቀመጡ፣ ለክስተቱ የዓይን ምስክር በሆነ ግለሰብ የተፈረመርባቸው እና መደበኛ ቅሬታዎችን መቀበል በሚቻልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረቡ መሆን አለባቸው።

## የፖሊስ መኮንኑን ስም እና የባጅ ቁጥር ሳላውቅ ቅሬታ ማቅረብ እችላለሁ?

አዎ፤ የDPD መዝገቦችን በመጠቀም መኮንኑን መለየት እንችላለን።

## ቅሬታ በማቅረቤ የአጸፋ ምላሽ ቢደርስብኝ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?

የአጸፋ ምላሽ ደርሶብኛል ብለው ከጠረጠሩ፣ በአስቸኳይ OCPOን ያነጋግሩ። ጉዳዩን ወደ DPD Internal Affairs Division የምናስተላልፍ ሲሆን፣ አስፈላጊ ከሆነ አዲስ ምርመራ ልንከፍትም እንችላለን።

## ቅሬታ ካቀረብኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

የእርስዎ ቅሬታ መድረሱን የሚያሳውቅ ደብዳቤ ከእኛ ጽሕፈት ቤት ወይም ከInternal Affair Division ይላክልዎታል።

በOCPO እና በDPD Internal Affair Division ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ጉዳዩ በእኛ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆን አለመሆኑን ይወስናሉ። የእርስዎ ቅሬታ በእኛ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ካልሆነ ክስተቱ እንዲመረመር ወደሚመለከተው ኤጀንሲ ወይም ተቋም ይተላለፋል። በእኛ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ከሆነ ቀጣይ የምንወስዳቸውን እርምጃዎች የሚገልጽ ደብዳቤ እንልክልዎታለን።

## ሥልጣን

OCPO በDPD አባላቶች ተፈጸሙ ከተባሉ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች ጋር የተያያዙ አሳሳቢ ክስተቶችን እና ቅሬታዎችን የመገምገም ወይም የመመርመር ሥልጣን አለው። ከDPD ውጪ በሆኑ የሌሎች ፖሊስ መምሪያዎች አባላት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ለሚመለከተው የአካባቢ መስተዳድር ወይም የስቴት ባለስልጣን መቅረብ አለባቸው።

## ቅሬታዎች የሚፈቱን እንዴት ነው?

እርስዎ ቅሬታዎን ካቀረቡ በኋላ OCPO እና የDallas Police Department Internal Affairs Division ከሚከተሉት ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን የምርመራ አይነት ለመወሰን ውንጀላዎቹን ይገመግማሉ፦

- **የቁጥጥር ቁጥር [Control Number (CN)] –** የጽሑፍ ተግሣጽ ወይም ከዚያ ከፍ የሚል ቅጣት ሊያስከትሉ ለሚችሉ ክሶች። እነዚህ ቅሬታዎች በInternal Affairs Division ይመረመራሉ።
- **የክፍል ሪፈራል [Division Referral (DR)] –** የቅጣት ምክር እና መመሪያ፣ በመዝገብ የሚያዝ የምክር አገልግሎት ወይም በአለቃ የተፃፈ

- **የክፍል ሪፈራል [Division Referral (DR)] የቀጠለ –** የማስተካከያ ቅጣት ሪፖርትን እና የመሳሰሉ እርምጃዎችን ሊያስከትሉ ለሚችሉ ቀለል ያሉ ውንጀላዎች። እነዚህ ቅሬታዎች ክስ የተመሰረተበት መኮንን አባል በሆነበት ክፍል ይመረመራሉ።
- **ምርመራ የማይደረግበት [No Investigation (NI)] –** በInternal Affairs Division ምንም ምርመራ ለማይደረግባቸው ጉዳዮች። ለምሳሌ ከ60 ቀናት በኋላ ለቀረቡ የሥነ-ምግባር ጥሰት ክሶች።
- **ሕዝባዊ ተዓማኒነት [Public Integrity (PI)] –** በፖሊስ መኮንኖች ከተፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ጋር ተያያዥ ለሆኑ ክሶች። እነዚህ ቅሬታዎች በPublic Integrity Unit (ሕዝባዊ ተዓማኒነት ክፍል) ይመረመራሉ።
- **ገለልተኛ ምርመራ –** OCPO አንዳንድ ጉዳዮች ላይ የራሱን ገለልተኛ ምርመራ በማከናወን ማስረጃ ሊያሰባስብ እና ግኝቶቹን ለCPOB ሊያቀርብ ይችላል።
- **ሽምግልና –** ሽምግልና ሲቪል ሰዎች እና የፖሊስ መኮንኖች ደኅንነቱ በተጠበቀ፣ ጸጥታ ባለበት እና ግላዊ በሆነ ስፍራ ላይ የሰለጠነ እና ገለልተኛ የሆነ አስታራቂ ባለበት ስለተፈጠረው ነገር በሚስጥር እንዲነጋገሩ ዕድል ይሰጣል። ሽምግልና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሂደት ነው፤ ሁሉም ወገኖች ለመስማማት መስማማት አለባቸው። በቅሬታ ቅጽዎ ላይ ሽምግልና እንዲደረግ መጠየቅ ይችላሉ።

## የቅሬታ ውጤቶች

ከምርመራ በኋላ በተሰበሰበው ማስረጃ ላይ በመመስረት የሚከተሉት ውሳኔዎች ይሰጣሉ፦

- **መሠረተ ቢስ ነው –** በቅሬታው ውስጥ ተፈጽመዋል የተባሉት ድርጊቶች አልተፈጸሙም።
- **ከወንጀል ነፃ ነው –** በቅሬታው ውስጥ ተፈጽመዋል የተባሉት ድርጊቶች የተከሰቱ ቢሆንም፣ ድርጊቶቹ ግን ፍትሐዊ፣ ሕጋዊ እና አግባብነት ያላቸው ነበሩ።
- **ተጨባጭ መረጃ የለም –** ክሶቹን ለማረጋገጥ ወይም ውድቅ ለማድረግ በቂ የሆነ ማስረጃ የለም።
- **ተጨባጭ ማስረጃ አለ –** በቅሬታው ውስጥ የተሰነዘሩትን ውንጀላዎች የሚደግፍ በቂ ማስረጃ አለ።
- **ተጠናቅቋል –** ምርመራው የአስተዳደራዊ ግምገማውን ዝርዝሮች ከተመለከተ በኋላ ምንም የደንብ ጥሰቶች አልተፈጸሙም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

## መድልዎ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት እንደተፈጸመ ካመኑ ምን ማድረግ ይችላሉ?

በሚቀጥሉት መንገዶች DPD ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፦

- **ኦንላይን፦** በ dal.city/OCPO ቅሬታዎን ያስገቡ።
- **በአካል፦** በDallas City Hall ወይም በማንኛቸውም የDPD መገኛዎች ይጎብኙን።
- **ኢሜይል፦** ወደ OCPO@dallas.gov ይላኩ።
- **ፖስታ፦** Dallas City Hall, 1500 Marilla St., 5DN, Dallas, TX 75201

ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾችን በDallas የሕዝብ ቤተመጻሕፍቶች፣ የመዝናኛ ማዕከላት፣ League of United Latin American Citizens (LULAC) እና National Association for the Advancement of Colored People (NAACP) ጽሕፈት ቤቶች በእንግሊዝኛ እና ስፓኒሽ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

## ሙሉ ምርመራ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

እያንዳንዱ ጉዳይ የተለያየ ነው። አንዳንድ ጊዜ አንድ ምርመራ በጥቂት ወራት ውስጥ በፍጥነት ሊጠናቀቅ ይችላል። አንዳንድ ምርመራዎች ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳሉ። ምርመራው የሚወስደው ጊዜ ተጎጂ የተባሉት ግለሰቦች እና ክስተቱ ላይ የተሳተፉ የፖሊስ መኮንኖች ብዛትን ጨምሮ ያሉት ምስክሮች እና የክስተቱ ውስብስብነትን የመሳሰሉ በርካታ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው።

## OCPO የፖሊስ መኮንኖች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል?

አይወስድም። ለሥነ-ምግባር ጥሰት የሚጣሉትን የዲሲፕሊን ቅጣቶች የሚወስኑት የፖሊስ አዛዥ (Chief of Police) ናቸው። ቅጣቶች በአስከፊነት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከሥራ እስከ መባረር ድረስ ሊደርሱ ይችላሉ። OCPO በዲሲፕሊን እርምጃው ካልተስማማ ለCity Manager (የከታማው ሥራ አስኪያጅ) ተጨማሪ እርምጃዎችን ሊጠቁም ይችላል።

## ቅሬታዎች በፖሊስ መኮንኖች መዝገብ ላይ ይቆያሉ?

አዎ። ውጤታቸው ምንም ይሁን ምን አንድ የፖሊስ መኮንን ላይ የቀረቡ ቅሬታዎች በሙሉ የፖሊስ መምሪያው የሠራተኞች መዝገብ አካል በሆነው የመኮንኑ ታሪክ ላይ ተቀምጠው ይቆያሉ። ይህም በሽምግልና ፕሮግራማችን በኩል የተፈቱ ቅሬታዎችን ያካትታል።

## OCPO በፍርድ ቤት መጥሪያዎች ወይም እስራት ረገድ እገዛ ያደርግልኛል?

አያደርግም፤ ይህንን ለማድረግ ሥልጣኑ የለንም። የፍርድ ቤት መጥሪያዎችን ወይም እስራቶችን መመልከት የሚችለው ፍርድ ቤት ብቻ ነው። ማንኛውንም ዓይነት ሕጋዊ ምክር ወይም እገዛ ማድረግ አንችልም። ፈቃድ ካለው የሕግ ጠበቃ መመሪያ ማግኘት ይኖርብዎታል።

## ቅሬታ ማቅረብ እንዴት ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ ይሆናል?

እርስዎ ቅሬታ በማቅረብ የDPDን ፖሊሲዎች እና አሠራሮች ለማሻሻል እገዛ ያደርጋሉ። የእርስዎ ጉዳይ ተሃድሶ እና ተጠያቂነት የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች በማጉላት ይበልጥ ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ግልጽነት ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር አስተዋጽዖ ያደርጋል።

የመድልዎ ወይም የሥነ-ምግባር ጥሰት ክስ ከማቅረብ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ጨምሮ OCPOን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ dal.city/OCPO ማግኘት ይቻላል።